# ለዋሺንግተን ሰራተኞች  የረጅም ጊዜ የእንክብካቤ ሽፋን በተመጣጣኝ ዋጋ

WA Cares Fund በመኖርያ ቤትዎ ራስዎን ችለው ዕድሜዎን እንዲገፉ  ለመርዳት የተነደፈ ጥቅማጥቅም ለማግኘት የሚረዳ ዘዴ  ነው። አብዛኛዎቻችን እንደ መታጠብ፣ መብላት፣ መንቀሳቀስ እና መድኃኒትን በአግባቡ ለመውሰድ የሚያስችለን  የረጅም ጊዜ እንክብካቤ ያስፈልገናል ግን ይህንን ወጭ የምንሸፈንበት  መንገድ የለንም።

Medicare እና የጤና መድኅን የረጅም ጊዜ እንክብካቤን አይሸፍንም ለMedicaid  ብቁ ለመሆን ደግሞ በተለምዶ በቁጠባ ያስቀመጡት የገንዘብ መጠን ከ $2,000 ያልበለጠ መሆኑን ማረጋገጥ ይጠይቃል። WA Cares በሕይወትዎ አስቸጋሪ ጊዜ በሕመምና በእርጅና አነዳይጎዱ  ተጨማሪ ምርጫዎችን  ለእርስዎ ለመስጠት አስፈላጊ ቁሶችን ያቀርባል።

## አሰራሩም

### በቋሚነት መዋጮዎን መክፍል

1



በሚሰሩባቸው ዓመታት የደመዎዝዎን 0.58% ያዋጣሉ።

### ለጥቅማጥቅሞች ብቁ  የሚሆኑት

2



ተገቢውን መዋጮ መክፈለዎንና የእንክብካቤ ፍላጎቶች መስፈርቶችን ማሟላትዎን ካረጋገጡ ለጥቅማጥቅሞች ያመልክቱ።

### ጥቅማጥቅሞችዎን ለማግኘት

3



የሚፈቀድልዎን $36,500 የህይወት ዘመን ጥቅማጥቅም መጠንን እንዴት እንደሚጠቀሙ ይምረጡ (ከዋጋ ግሽበት ጋር አብሮ ይጨምራል)።

## ለጥቅማጥቅሞች ብቁ ለመሆን

ጥቅማጥቅሞችን ለመድረስ ሁለት መስፈርቶችን ማሟላት አለብዎት።

እንክብካቤ ሲያስፈልግዎት ጥቅማጥቅሞችን በየትኛውም ስቴት ሁነው  ለመቀበል ይችላሉ።

### 1. የማበርከቻ መስፈርት

የማበርከቻ መስፈርቱን ከሦስት መንገዶች በአንዱ በኩል ማሟላት ይችላሉ።

- **ቋሚ መንገድ፦** ቢያንስ ለ10 ዓመት መዋጭዎን በመክፈል ሙሉ ከፈያውን ያገኛሉ ።*
- **ጊዜያዊ መንገድ፦** ለጥቅማጥቅም በሚያመለክቱበት ጊዜ ካለፉት ስድስት ዓመታት* ውስጥ ቢያንስ ለሦስት ካበረከቱ የሙሉ ጥቅማጥቅም መጠን ያግኙ።
- **የሽግግር መንገድ፦** ከ1968 በፊት ከተወለዱ ላበረከቱት እያንዳንዱ ዓመት* የሙሉ ጥቅማጥቅሙን 10% የህይወት ዘመን መዳረሻ ያግኙ።

*ቢያንስ 500 ሰዓታት የሚሰሩበትን እያንዳንዱን ዓመት እንቆጥራለን።

### 2. እንክብካቤ መስፈርት ያስፈልገዋል

በዕለታዊ ኑሮ ሦስት ወይም ከዚያ በላይ እንቅስቃሴዎች ላይ እገዛ እንደሚያስፈልግዎት እና ቢያንስ ለ90 ቀናት እገዛ ማስፈለጉ እንደሚቀጥል ማረጋገጥ አለብን። የምንገመግማቸው እንቅስቃሴዎች የሚከተሉት ናቸው፦

- መታጠብ
- አልጋ ላይ የመንቀሳቀስ ችሎታ
- መተላለፍ (ወንበር ላይ መቀመጥ ወይም ከወንበር መነሳት)
- ሽንት ቤት መጠቀም
- እንቅስቃሴ (መራመድ ወይም መንቀሳቀስ)
- መብላት
- መድኃኒቶችን በአግባቡ መውሰድ

ማንኛውንም እንቅስቃሴዎች ሙሉ በሙሉ በራስዎ መፈጸም ካልቻሉ እና የሌላ ሰው ክትትልና እርዳታ የሚፈልግ ከሆነ ይቆጠራል (እንደ መከታተል፣ ምልክት መስጠት ወይም እርዳታ ማሰናዳት ያሉ)።

# ለጥቅማጥቅሞች ማመልከት

ሂደቱን ለመጀመር እርስዎ (ወይም የሚረዳዎት ሰው) የሚከተለውን ድረ-ገጽ በመጎብኘት የWA Cares ጥቅማ ጥቅም አካውንትን መክፈት ይችላሉ wacaresfund.wa.gov/apply።

መስፈርቱን እንዳሟሉ ካረጋገጥን በኋላ ስለ እንክብካቤ ፍላጎቶችዎ ለማውራት በአካል ቀጠሮ ያስይዛሉ። ከዚያም ጥቅማጥቅሞቹን ለመጠቀም ፈቃድ ማግኘት ወይም አለማግኘትዎን እናሳውቅዎታለን።

የበለጠ ለመረዳት wacaresfund.wa.gov/benefits ይጎብኙ።

# ጥቅማጥቅሞችዎን መጠቀም

ከWA Cares አቅራቢ ማናቸውንም ሽፋን ያላቸውን አገልግሎቶችና ጥቅማጥቅሞች ለማግኘት  ይችላሉ።

## እርስዎ ቤት እንዲቆዩ ለማገዝ

- ከግል አቅራቢ ወይም የቤት ለቤት እንክብካቤ ኤጀንሲ የቤት ውስጥ እንክብካቤ የቤት ደህንነት ግምገማዎች
- የቤት ውስጥ ደህንነት ግምገማ
- የቤት ማሻሻያዎች
- ወደ ቤት የሚላኩ ምግቦች
- ትራንስፖርት
- ተዛማጅ መሣሪያ እና ቴክኖሎጂ
- የግል የድንገተኛ ጊዜ ምላሽ ሥርዓቶች
- የቤት ውስጥ እና የአትክልት ሥራ

## የቤተሰብ እንክብካቤ ስጭውን ስለመደገፍ

- ባለቤትን ወይም የቅርብ ቤተሰብን በመክፍል እንክብካቤ መስጠት
- በቤትዎ ወይም ተቋም ውስጥ የእረፍት ጊዜ እንክብካቤ
- እንክብካቤዎን ለማስተዳደር እንዲያግዝ ትምህርት እና ምክር
- ዲሜንሻ እና የባህሪ ድጋፎች
- ከተቋም ወይም ሆስፒታል ሲወጡ እርስዎን መደገፊያ የእንክብካቤ ሽግግር ቅንጅት

## በማህበረሰብዎ ውስጥ

- የአዋቂ ቤተሰብ ቤት አገልግሎቶች
- የአዋቂ የቀን አገልግሎቶች

## በተቋም ውስጥ

- የማስታወስ ችሎታ እንክብካቤ አገልግሎቶችን ጨምሮ እርዳታ የሚደረግባቸው የመኖሪያ አገልግሎቶች
- የአረጋውያን መንከባከቢያ ቤት አገልግሎቶች

አንዳንድ አገልግሎቶች በግዛቱ/በስቴቱ በሁሉም ቦታ ላይገኙ ይችላሉ።

# ድጋፍ ያግኙ

ከሰኞ እስከ አርብ ከ8:30 ኤኤም እስከ 4:30 ፒኤም ሊያነጋግሩን ይችላሉ። (የስቴት በዓላት ላይ ይዘጋል)። ለቅርብ ጊዜ መረጃ wacaresfund.wa.gov ይጎብኙ።

### ስልክ

844-CARE4WA (844-227-3492)

### ኢሜይል ወይም በጽሁፍ

wacaresfund.wa.gov/contact ይጎብኙ

ለTTY/ TDD ወይም Washington Relay Service 711 ላይ ይደውሉ። የቋንቋ እርዳታ በስልክ ወይም ኢሜይል ይገኛል።